

# አናንሲና ጥበብ

Ghanaian folktale
Wiehan de Jager
Mezemir Girma
Amharic
Level 3



በድሮ ዘመን ሰዎች ምንም አያውቁም ነበር። ሰብል እንዴት እንደሚዘራ፣ ሸመናም ሆነ የአንጥረኝነት ስራ እንዴት እንደሚሰራ ምንም ሃሳብ አልነበራቸውም። በሰማይ ያለው ንያሜ የተባለው አምላክ ግን የዓለምን ሁሉ ጥበብ ይዞ ነበር። በአንድ ገንቦም ውስጥ በጥንቃቄ አስቀምጦት ነበር።



ከዕለታት አንድ ቀን ንያሜ ይህን የዕውቀት ገምቦ ለአናንሲ ለመስጠት ወሰነ። አናንሲ የሸክላውን ገንቦ ባየ ቁጥር አንድ አዲስ ነገር ያገኝ ነበር። ያስደስት ነበር!



ገብጋባው አናንሲ ‹‹ይህን ገንቦ በአንድ ትልቅ ዛፍ ጫፍ በጥንቃቄ አስቀምጠዋለሁ። ከዚያም ሁሉም የኔው ይሆንልኛል!›› ሲል አሰበ። አንድ ረጅም ክርም ገምዶ በሸክላው ገንቦ ዙሪያ አሰረ፤ ከዚያም በሆዱ ዙሪያ ጠመጠመ። ዛፉንም መውጣት ጀመረ። ገንቦው አሁንም አሁንም ጉልበት ጉልበቱን እየመታው ዛፍ መውጣቱ ከበደው።



ይህን ሁሉ ጊዜም የአናንሲ ትንሽ ልጅ ከዛፉ ስር ቆሞ እየተከታተለው ነበር። እሱም ‹‹አዝለኸው ብትወጣ አይሻልም ወይ?››አለው። አናንሲ ጥበብ የያዘውን የሸክላ ገንቦ ከጀርባው ለማሰር ሞከረ፤ እውነትም አመቺ ነበር።



ባጭር ጊዜም ከዛፉ ጫፍ ደረሰ። እዚያም ቆም አለና ‹‹ይህ ሁሉ ዕውቀት የኔ እንዲሆን ነው የተፈለገው፤ ግን ይሄው ልጄ ከኔ የበለጠ ብልህ ሆነ!›› በማለት አሰበ። አናንሲ በዚህ በጣም ተናዶ ያንን የሸክላ ገንቦ ከዛፉ ላይ ወደ ታች ወረወረው።



መሬትም ላይ ወድቆ ፍርክስክሱ ወጣ። ጥበብም ለማንኛውም ሰው በእኩል ተዳረሰ። በዚህም ምክንያት ነበር ሰዎች እርሻ፣ ሽመና፣ አንጥረኝነትና ሌሎችንም ሰዎች መስራት የሚችሏቸውን ነገሮች ሁሉ የተማሩት።

# Storybooks Outline

global-asp.github.io/storybooks-outline

## አናንሲና ጥበብ

Written by: Ghanaian folktale
Illustrated by: Wiehan de Jager
Translated by: Mezemir Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Outline in an effort to provide children’s stories in the world’s many languages.

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 3.0 International License.